# ወደ Unlawful Detainer (Eviction) (ንብረትን በሕገ ወጥነት ለያዘ ሰው (ከቤት እንዲወጡ ማድረጊያ)) ችሎትዎ መሄድ

❖ በ Washington (ዋሽንግተን) ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ብቻ ይህንን ያንብቡ።

❖ እኛ የምናገናኛቸውን ሁሉንም የዋና ዋና ነጥቦች መረጃ እዚህ በ WashingtonLawHelp.org ላይ ማግኘት ይችላሉ።

❖ **ኮሮናቫይረስ/COVID-19 ወቅታዊ መረጃ**: እስከ ኦገስት 1 ድረስ፣ የቤት አከራይዎ ከቤቱ ሊያስወጣዎት የሚችለው በተወሰኑ ምክንያቶች ብቻ ነው። ይህንን ያንብቡ ኮሮናቫይረስ (COVID-19): ችግር እየፈጠሩ ካልሆነ፣ ወይም አከራይዎ ቤቱን ሊኖርበት ወይም ሊሸጠው ካልፈለገ በቀር በዚህ ቀውስ ወቅት ከቤትዎ እንዲወጡ ሊደረጉ አይችሉም።

## ይህንን መጠቀም አለብኝ?

አዎ፣ የሚከተሉት ሁለቱም ነገሮች ትክክል ከሆኑ፡

1. የቤት አከራይዎSummons and Complaint for Unlawful Detainer (ንብረትን በሕገ ወጥነት ለያዘ ሰው መጥሪያ እና ቅሬታ ማቅረቢያ) ቅጽ ሰጥቶዎታል።

2. ቢያንስ Notice of Appearance (የመቅረቢያ ማስታወቂያ) በማስገባት ምላሽ ሰጥተዋል። ከቤት የማስወጣት ጥያቄውን ለመሞገት አቅደዋል።

## Show Cause (ምክንያትን/ማስረጃን ማቅረቢያ) ችሎት ምንድን ነው?

ከመጥሪያ እና ቅሬታ ማቅረቢያው ጋር **ምክንያትን የማቅረቢያ ትዕዛዝ** ደርሶዎት ከሆነ፣ ይህ ማለት የቤት አከራይዎ ሁኔታው በፍርድ ቤት እንዲታይ አስቀጥረዋል ማለት ነው። ይህንን ችሎት **ምክንያትን የማቅረቢያ ችሎት**ብለንእንጠራዋለን።

ምክንያትን የማቅረቢያ ትዕዛዝ ከደረሰዎት እና ከቤት የማስወጣት ጥያቄውን ለመሞገት ከፈለጉ፣ **ወደ ችሎት መሄድ አለብዎት**። የሚከተለውን ብቻ ማድረግ በቂ አይደለም

- የመቅረቢያ ማስታወቂያዎን ወይም መልስ (Notice of Appearance or Answer) ማቅረብ

- ኪራይዎን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ጸሃፊው (Superior Court Clerk) ማቅረብ **ወይም** የቃለመሃላ መግለጫ ማስገባት

## ችሎቱ የሚደረገው መቼ እና የት ነው?

ቀኑ እና ሰዓቱ ምክንያትን የማቅረቢያ ትዕዛዙ ላይ ይገለጻል። **በችሎቱ ላይ በሰዓቱ መገኘት አለብዎ!**

## ምክንያትን የማቅረቢያ ችሎት ላይ ምን ይፈጠራል?

ከቤት የማስወጣት ጥያቄውን ለመሞገት ጥሩ መከላከያ ካለዎት፣ በዚሁ መሰረት ዳኛው ወይም ኮሚሽነሩ ውሳኔውን ይወስናል። እዚያው ላይ ጉዳዩን ሊያሸንፉ ይችላሉ። ወይም ደግሞ እራስዎን ለመከላከል እንዲችሉ ዳኛው ሙሉ የፍርድ ሂደት እንዲደረግ ሊፈቅዱልዎ ይችላሉ።

የመከላከያ ነጥቦችዎ ጠንካራ አይደሉም ብሎ የሚያስብ ዳኛ የሚከተሉትን ሊወስን ይችላል

- የቤት አከራይዎ ወዲያውኑ ከቤቱ ሊያስወጣዎት እንደሚገባ
- ለቤት አከራይዎ መክፈል ያለብዎ ምን ያህል ዕዳ አለብዎ

የቤት አከራይዎ የህግ ጠበቃ አከራይዎ ለምን ከቤት ሊያስወጣዎት እንደሚገባ አጠንክሮ ሊከራከር ይችላል። ከዛም እርስዎ ደግሞ ለምን ከቤትዎ ሊያስወጡዎት እንደማይገባ ይከራከራሉ።

## ለችሎቱ መዘጋጀት ያለብኝ እንዴት ነው?

1. ስለጉዳይዎ በሚገባ ለመከራከር የሚያስችሉዎትን ሁሉንም አስፈላጊ ወረቀቶች ወይም ሰነዶች ያዘጋጁ። ይህም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡

    ☐ የሊዝ ወይም የኪራይ ውልዎ

    ☐ የመጠባበቂያ ተቀማጭ ገንዘብ ደረሰኝዎ

    ☐ ሲገቡበት ቤቱ የነበረበት ሁኔታ የማረጋገጫ ዝርዝር

    ☐ በቤቱ ውስጥ ያሉ ችግር ያለባቸው ነገሮች ዝርዝርዎ

    ☐ የኪራይ ክፍያ ደረሰኞች እና የተሰረዙ ቼኮች

    ☐ ከቤት የማስወጫ ማስታወቂያዎች

    ☐ መጥሪያ እና ቅሬታ ማቅረቢያ

☐ ለቤት አከራይዎ ጠበቃ እና ለፍርድ ቤቱ ያስረከቡበት ቀን የተጻፈበት ማህተም ያለው የመቅረቢያ ማስታወቂያ ወይም መልስ የእርስዎ ቅጂዎች፣

☐ በቦታው ላይ ለደረሱ ጉዳቶች ጥገና የሚያስፈልግ የግምት መጠን በጽሁፍ

☐ በቦታው ላይ እርስዎ ላደረጉት የጥገና ስራ የከፈሉበት ደረሰኝ

☐ በቦታው ላይ ያሉ ማንኛውንም አይነት ችግሮች የሚያሳዩ ፎቶዎች

---

- ❖ ከቻሉ የሰነዶቹን ዋና ቅጅዎች ይዘው ይቅረቡ። ፍርድ ቤቱ ምናልባት ማስቀረት ከፈለገ፣ ተጨማሪ ቅጂዎችን ይዘውይቅረቡ።

- ❖ አንድን ነገር እንደሚፈልጉት ወይም እንደማይፈልጉት እርግጠኛ ካልሆኑ፣ ለማንኛውም ይዘውት ይቅረቡ!

---

**2.** ጉዳይዎን በችሎቱ ላይ በማቅረብ ሊረዳዎት የሚችል ማንኛውንም ምስክር ካለ በቦታው እንዲገኙ ይጠይቋቸው። ምስክሮቹ በእርስዎ እና በቤት አከራይዎ መካከል ያለውን የጉዳት ወይም አለመግባባት ሁኔታ በአካል የተመለከቱ መሆን አለባቸው። ስለ ጉዳይዎ ሁኔታ በግል ዕውቀት ያላቸው ብዙ ምስክሮች ከቀረቡ ለጉዳይዎ የተሻለ ይሆናል።

**3.** ከችሎትዎ በፊት ስርዓቱ እንዴት እንደሚሰራ ይመልከቱ። ፍርድ ቤቱ “ምክንያት/ማስረጃ ማቅረብ” የተመለከቱ ችሎቶችን መቼ እንደሚያይ የፍርድ ቤት ጸሃፊውን ይጠይቁ። የእርስዎ ጉዳይ እንዴት እንደሚሆን ለማወቅ በችሎት ላይ ተቀምጠው ሂደቱን ይመልከቱ።

**4.** ችሎቱ ከመካሄዱ በፊት፣ ለመናገር የሚፈልጉትን ነገር በሚገባ ይለማመዱ። የሚያቀርቡት ነገር በአግባቡ የተደራጀ እና አጭር መሆን አለበት። አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦችን ዝርዝር ያዘጋጁ።

**5.** ለምስክሮችዎ ምን እንደሚጠይቋቸው አስቀድመው ያሳውቋቸው።

## እንግሊዝኛ የማልናገር ከሆነስ ምን ማድረግ አለብኝ?

እንግሊዝኛ የማይናገሩ ከሆነ ወይም የመናገር ወይም የመስማት ችግር ካለብዎ፣ በፍርድ ቤት ውስጥ አስተርጓሚ የማግኘት መብት አለዎት። አስተርጓሚ እንደሚፈልጉ **ለፍርድ ቤቱ በተቻለ መጠን ቀደም ብለው ማሳወቅ አለብዎት።**

## ለችሎቱ መሄድ ያለብኝ ወዴት ነው?

ፍርድ ቤት እንደደረሱ፣ ወዴት መሄድ እንዳለብዎ ለማወቅ የፍርድ ቤቱን ጸሃፊ ያነጋግሩ። የፍርድ

ቤቱ ጸሃፊ ወዴት መሄድ እንዳለብዎ ይነግርዎታል። ፍርድ ቤቱ በእለቱ የሚያያቸውን ጉዳዮች ዝርዝር ከፍርድ ቤቱ ውጭ ይለጥፋቸዋል **ወይም** ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት ዝርዝራቸውን ሊያነቡ ይችላሉ። የእርስዎን ጉዳይ ካልለጠፉት ወይም ካላነበቡት፣ የፍርድ ቤቱን ጸሃፊ ያነጋግሩ።

## በችሎቱ ላይ ምን ይፈጠራል?

ብዙውን ጊዜ ዳኛው ሂደቱን የሚጀምረው የፍርድ ቤቱን አሠራር በመግለጽ ነው። ከዛም የመጀመሪያውን ባለጉዳይ ይጠራሉ።

ዳኛው የእርስዎን ጉዳይ ሲያሳውቁ፣ ማስረጃዎችዎን እና ምስክሮችዎን በመያዝ ወደፊት ይቅረቡ። ብዙውን ጊዜ ከሳሾች፣ ተከሳሾች፣ እና ምስክሮች ቃላቸውን ከመስጠታቸው በፊት እውነቱን ለመናገር መሃላ መፈጸም አለባቸው

## በችሎቱ ላይ ምን ማለት አለብኝ?

1. የቤት አከራይዎ ለምን ከቤት ሊያስወጣዎት እንደማይገባ ያብራሩ። ባለንብረቱ አስፈላጊውን ጥገና ካላደረገ፣ የቤት ኪራይ ከፍለው እያለ አከራዩ ግን አልከፍሉም ካለዎት፣ የአከራይ ተከራይ ደንቡን ለመቀየር ተገቢው ማስታወቂያ ካልሰጠዎት፣ ወይም ማንኛውንም ማስታወቂያ ዘግይቶ ከሰጠዎት እነዚህን ሁኔታዎች ለፍርድ ቤቱ ይግለጹ። ለጥገና ስራዎች ከኪራይዎ ላይ ቀንሰው ከፍለው ከሆነ፣ ይህንኑ ይግለጹ።

2. ይዘው የመጡትን ማንኛውንም ማስረጃ ለዳኛው ያሳዩ። ከላይ “ለችሎቱ መዘጋጀት ያለብኝ እንዴት ነው” የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።

3. ምስክሮች ካሉዎት፣ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ እንደሚፈልጉ ለዳኛው ይግለጹ። የቤት አከራይዎ ለምን ከቤት ሊያስወጣዎት እንደማይገባ ይጠይቋቸው።

የቤት አከራይዎ የቤት ኪራይ ባለመክፈልዎ ከቤት ሊያስወጣዎት እየሞከረ ከሆነ፣ ክፍያ የሚፈጽሙበትን እቅድ ለማውጣት እንዲችሉ ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላሉ። በ RCW 59.18.410(2) መሰረት የተከራይና አከራይዝ ውል መልሶ ለማስቀጠል ሃሳብ ማቅረብ እና የተገደበ ስርጭት ትዕዛዝ ቅፅንይጠቀሙ።

## ዳኛው ውሳኔውን የሚያሳውቁት መቼ ነው?

የሁለቱንም ወገኖች ሃሳብ ከሰሙ በኋላ፣ ዳኛው ከሚከተሉት መካከል አንዱን ሊወስኑ ይችላሉ፡

1. **በእርስዎ ላይ ይፈረድብዎታል**። በቂ የሆነ መከላከያ እንደሌለዎት ዳኛው ይወስናሉ። ሸሪፍ እርስዎን ከቤትዎ እንዲያስወጣዎ ዳኛው ያዛሉ። ለቤት አከራይዎ ሊከፍሉት የሚገባ የገንዘብ ዕዳ እንዳለብዎ ዳኛው ሊወስኑ ይችላሉ። ለቤት አከራይዎ ምን ያህል ገንዘብ መክፈል እንዳለብዎ ዳኛው ሊወስኑ ይችላሉ፣ ወይም ይህንን ውሳኔ ብሌላ ጊዜ ሊወስኑ

ይችላሉ።

2. **ለእርስዎ ይፈረድልዎታል**። ከቤት የማስወጣቱን ጥያቄ ላለመቀበል በቂ የሆነ መከላከያ እንዳቀረቡ ዳኛው ይወስናሉ። ዳኛው ጉዳዩን ውድቅ ያደርጉታል። ቢያንስ ለጊዜው ከቤት መውጣት የለብዎትም። የቤት አከራይዎ ከቤት ለማስለቀቅ ትክክለኛውን አካሄድ ስላልተከተሉ ዳኛው ይህንን ውሳኔ ሊያስተላልፉ ይችላሉ። ከቤት በማስለቀቅ ሂደት ላይ የፈጠሯቸውን ስህተቶች ካስተካከሉ በኋላ፣ የቤት አከራይዎ ቤቱን ሊያስለቅቁዎ ይችሉ ይሆናል።

3. **ዳኛው በውሳኔው ላይ ብይን ለመስጠት ይችሉ ዘንድ ሙሉ የፍርድ ሂደት ያስፈልጋቸዋል**። የፍርድ ቤት ቀጠሮ ይሰጥዎታል። በአሁኑ ወቅት በቤቱ ውስጥ እየኖሩ ከሆነ፣ በ 30 ቀናት ውስጥ የፍርድ ሂደት ይሰጣል።

## ጉዳዬን በርካታ ዳኞች ሊመለከቱት ይችላሉ?

ይህ "ምክንያትን በማቅረቢያ ችሎት" ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

ዳኛው ሙሉ የፍርድ ሂደት ካዘዙ ግን የዳኝነት ሂደቱን በበርካታ ዳኞች የማግኘት መብት አለዎት። በዚህ መንገድ ብይን እንዲሰጥዎት ከፈለጉ፣ እባክዎ ለዚሁ አገልግሎት መክፈል ሊኖርብዎ እንደሚችል ልብ ይበሉ። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የፍርድ ቤቱን ጸሃፊ ያነጋግሩ።

## በምክንያት ማቅረቢያ ችሎቱ ላይ ሳልገኝ ብቀርስ?

ሳይገኙ ከቀሩ ወይም ደግሞ በጥቂት ደቂቃዎችም ቢሆን ዘግይተው ከደረሱ፣ ውሳኔው በእርስዎ ላይ ሊወሰንብዎ ይችላል። ዳኛው የቤቱ ባለቤት ከቤቱ እንዲያስወጣዎ ይፈርዳሉ። ሸሪፉ ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ያስገድድዎታል። የቤቱ ባለቤት አለባቸው ብለው የጠየቁትን ክፍያ ሁሉ መክፈል ሊኖርብዎ ይችላል። ይህም የቤት ኪራይን፣ የደረሱ ጉዳቶችን፣ የፍርድ ቤት ወጪዎችን፣ እና የጠበቃ ክፍያን ሊያካትት ይችላል።

## የቤቱ ባለቤት ቤቱን ለቅቄ እንድወጣ በጉልበት ሊያስገድዱኝ ይችላሉ?

**በፍጹም**። ከመኖሪያ ቤትዎ በጉልበት አስገድዶ ሊያስወጣዎት የሚችለው **ሸሪፉ ብቻ ነው**። በጉዳዩ ላይ ሸሪፉ እንዲሳተፉ ለማድረግ የቤቱ አከራይ ፍርድ ቤት መሄድ አለባቸው።

## በምክንያትን በማቅረቢያ ችሎት ላይ "ከቤት የማስወጫ ቀጠሮ" ተቀብያለሁ። እንዲህም ሆኖ ከመኖሪያ ቤት የመውጣቴን ሁኔታ ማስቀረት እችላለሁ?

ምናልባት አይችሉ ይሆናል። እዚህ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ እንዲወጡ መድረግዎን ማስቆም በጣም ከባድ ነው። በማስወጣት ሂደቱ ላይ የቤት አከራዩ ስህተት የሆነ ነገር ካደረጉ፣ ቤቱን እንዲለቁ የመድረግዎን ሂደት ማስቆም ይችሉ ይሆናል። ወዲያውኑ የሕግ እርዳታ ለማግኘት ይሞክሩ።

**ከቤት እንዲወጡ የተደረጉት ያልከፈሉት የቤት ኪራይ ክፍያ በመኖሩ ከሆነ፣** ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን በእርስዎ ላይ በበየነ በ 5 ቀናት ውስጥ ያለብዎትን እዳ በሙሉ (የበፊት የኪራይ ክፍያ፣ የፍርድ ቤት ወጭዎች፣ እና የጠበቃ ክፍያዎች) ከከፈሉ፣ የሊዝ ውልዎን "ማስመለስ" (ተከራይነትዎን ማስጠበቅ) ይችሉ ይሆናል። ይህንን ለማድረግ ሸሪፍ ከቤትዎ ሊያስወጣዎት ከመምጣቱ በፊት ለፍርድ ቤቱ መደበኛ ጥያቄ ማቅረብ ("ሃሳብ ማቅረብ") አለብዎት። በ RCW 59.18.410(2) መሰረት የተከራይና አከራይዝ ውል መልሶ ለማስቀጠል ሃሳብ ማቅረብ እና የተገደበ ስርጭት ትዕዛዝ ቅፅን ይጠቀሙ።

ከዚህም ሌላ የክፍያ እቅድ በመጠየቅ ሁኔታው እንዲታይልዎ "ሃሳብ ማቅረብ" ይችላሉ። በ RCW 59.18.410(3) መሰረት ከቤት የማስወጫ ቀጠሮን በማስቀረት መቆየት እንዲቻል ሃሳብ ማቅረብ እና የክፍያ እቅድ ቅፅን ይጠቀሙ።

## እነዚህ የሚቀርቡ ሃሳቦች ውስብስብ ናቸው። በተቻለ ፍጥነት የሕግ ድጋፍ ለማግኘት ይሞክሩየሕግ ድጋፍ ያግኙ

**ከ King County (ኪንግ ካውንቲ) ውጭ፣** በ CLEAR ሆትላይን 1-888-201-1014 በስራ ቀናት ከ 9:15 am - 12:15 pm ባለው ጊዜ ውስጥ ይደውሉ። አስተርጓሚዎች ይቀርባሉ።

**በ King County (ኪንግ ካውንቲ) ውስጥ፣** በስልክ ቁጥር 2-1-1 በስራ ቀናት ከ 8:00 am - 6:00 pm ባለው ጊዜ ውስጥ ይደውሉ። ወደ የሕግ ድጋፍ አቅራቢ ይመሩዎታል።

**እድሜዎ 60 ዓመት ወይም ከዛ በላይ ከሆነ፣** በሃገር አቀፍ ደረጃ ወደ CLEAR*Sr በ 1-888-387-7111 መደወል ይችላሉ።

ከዚህ በተጨማሪም፣ በ CLEAR*Online: nwjustice.org/get-legal-help በኦንላይን ማመልከት ይችላሉ።

---

ይህ ጽሑፍ መብቶችዎን እና ኃላፊነቶችዎን በተመለከተ አጠቃላይ መረጃን ይሰጣል። ለተወሰነ የሕግ ምክር ምትክ ሆኖ የታሰበ አይደለም።

**© 2020 Northwest Justice Project — 1-888-201-1014.**

(የመገልበጥ እና የማሰራጨት ፈቃድ ለንግድ ላልሆነ አላማ ብቻ ለ Alliance for Equal Justice (አሊያንስ ለእኩል ፍትህ) እና ለግለሰቦች ተሰጥቷል።)